# ውሃ ቆጣቢ የእጅ መታጠቢያ የማዘጋጀት ቅደም ተከትል፡፡



















1. ውሃ ቆጣቢ የእጅ መታጠቢያ ለማዘጋጀት በአቅራቢያዎ በቀላሉ የሚገኝ ዕቃ ለምሳሌ እንደ ፕላስቲክ ጠርሙስ፣ አሮጌ ጀሪካን፣ ቶፋ ወይም ቅል ያዘጋጁ፡፡ በተዘጋጀው ዕቃ ላይ ለውሃ ማውረጃ ቀዳዳ ለማውጣት ሚስማር ወይም ወስፌ ያዘጋጁ፡፡

2. በተጨማሪም ለውሃ ማወረጃ የሚሆን እንድ እስክርቢቶ፣ ቀፎ፣ የሸንበቆ ቀሰም ወይም እንደ ቀሰም ያለ ነገር ያዘጋጁ፡፡ ያዘጋጁት የውሃ መያዥያ፣ የእስክርቢቶ ቀፎ፣ የሸንበቆ ቀሰም ወይም ቀሰም ከቆሻሻ፣ ከዘይትና ከላምባ የፀዳ ስለመሆኑ ያረጋግጡ፡፡

3. የእጅ መታጠቢያ የሚቀመጥበትን ቦታ ይወስኑ፡፡ መታጠቢያው መቀመጥ ወይስ መንጠልጠል ወይንስ ተንጠላጣይና ያጋደለ መሆን አለበት የሚለውን ይወስኑ፡፡

4. ከእስክሮቢቶ ቀፎ ወይም ቀሰም ያዘጋጁት የውሃ ማፍሰሻ መያዣው ላይ ለመሰካት እንዲቻል በቅድሚያ በሚዘጋጀው የመታጠቢያ ዕቃ ላይ ቀዳዳ ማበጀት ይስፈልጋል፡፡ ቀዳዳ ለማበጀት ሚስማሩን ወይንም ወስፌውን በእሳት ያግሉት፡፡ ከዕቃው መቀመጫ ወይም ቂጥ 2 ሳንቲ ሜትር ወይም 2 ጣት ከፍ በማለት በአጋሉት ሚስማር ወይም ወስፌ ዕቃውን በጥንቃቄ ይብሱት፡፡

5. ጀሪካን ወይንም ቅል የሚጠቀሙ ከሆነ የእስክርቢቶው ቀፎ ወይም ቀሰም በቀዳዳው ውስጥ በዝግታና በጥንቃቄ ያስገቡት፡፡ የእስክርቢቶን ቀፎ በሚገፋበት ግዜ ቀዳዳው ሰፍቶ ውሃ እንዳያንጠባጥብ በጣም መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ውሃ በምንም ዓይነት እንዳይንጠባጠብ ውሃ መውረጃውን ዙሪያውን በሙጫ፣ በታኘከ ማስቲካ ወይም እጣን ይዝጉት፡፡ የውሃ ማውረጃውን ቀዳዳ መወተፊያ ከእንጨት ወይም ከተመሳሳይ ነገር መስራት ይቻላል፡፡ የእስክርቢቶውን ቀፎ ክዳን ወይም መወተፊያ ሲነቅሉት ውሃ ያወርዳል፡፡

6. የውሃ መያዥያ ፕላስቲክ ጠርሙስ የሚጠቀሙ ከሆነ የፕላስቲኩ ክዳን ሲከፈት ውሃው ይወርዳል ክዳኑን ሲዘጉት ደግሞ ውሃ መውረድ ይቆማል፡፡ ስለዚህ ቀዳዳ ብቻ ማበጀት እንጂ እስክርቢቶ ወይንም ቀሰም መጠቀም አያስፈልግም

USAID FROM THE AMERICAN PEOPLE | HIP HYGIENE IMPROVEMENT PROJECT

wsp water and sanitation program

ውሃ ቆጣቢ የእጅ መታጠቢያ ማዘጋጀት በቂ የውሃ አቅርቦት ባይኖርም እንኳ እጅን አስፈላጊ በሆነበት ሰዓት ለመታጠብ ይረዳል